የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሄራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY

ዓመታዊ ዘገባ፡-

ከኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነትና ከኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ

የቀረበ ዓመታዊ ዘገባ፡-

ሁለቱ የፖለቲካ ድርጅቶች የጋራ የትጥቅ ትግል በጣምራ ከጀመሩ እነሆ ዓመት ሞላቸው። በዚህ የ፩ ዓመት ትግል ውስጥ ያከናወኗቸውና ያደረጉት ገድሎች በጣም የጎሉና አመርቂ ናቸው ብለን ባናወሳም አንድ ነገር መወርወር የሰመረ ጅማሮ ለአኩሪ ግብ እንደሚያደርሰን በእርግጠኝነት በመተማመን ይህንን የዓመቱን ክንውኖች እናቀርባለን። ትግላችን በአንድ ጎን ብቻ የሚንቀሳቀስ ሣይሆን በሁሉም መስክ የተደረገ ሲሆን ጠላት ወያኔንን ጥለው የወደቁ ጀግኖቻችንን የምንዘክርበት የዓመቱ ቀን ሲሆን በሕይወት ኑረው ጠላት ወያኔን በአንድ እግር ያንጠለጠሉትን ጀግኖች ወንድሞቻችንን የምናበረታታበት ክቡር ቀን ነው።

ሁለቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ይህን የትጥቅ ትግል ስልት የመረጡበት ዋና ምክንያት ጠላት የትግሬ ወያኔ ከሚለፍፈውና ለ27 ዓመት በተግባር እያዋለ ለውን ሀገር አፍራሽ ድርጊት ለማስቆምና ብሎም

ከኢትዮጵያ አገዛዝ ለማስወገድ ነው። የነኝህ የሁለቱ የፖለቲካ ድርጅቶች ትግሉን በተግባር ማሳየትን በተመለከተ የቀድሞ ሠራዊት አባላት ኮሚቴ እንደ አስፈላጊነቱ ከጎናችን በመሆን ትግሉ እንዲጎለብት ጥረቱን በተግብባር ማሳየቱ ነው። የቀድሞ ሠራዊት አባሎች የዳበረ እውቀታቸውን ለማካፈል

ከጎናችን በመሰለፋቸው ትግሉ የበለጠውን እንዲጠናከርና ከፍተኛ ሥነልቦናዊ ብርታትን እንዲቀዳጅ እረድቶታል።

ዛሬ ትልቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጠላት ወያኔ ነው ቢባልም በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ለትግሉ እንቅፋት የሆኑ ከተቃዋሚዎችም ጎራ እንዳሉ የሚታወቅ ነው።

ይህንንም  ዛሬ ሪፖርታችን ለጊዜው የሚያተኩረው አመታዊ ዘገባ ላይ ቢሆንም ወደመጨረሻው ላይ ሳንጥቅስ ግን አናልፍም።

የትግሬ ወያኔ በትጥቅ እንቅስቃሴው ወቅት በኢትዮጵያ ሕዝብ ድጋፍ ሥልጣን እንደተቆናጠጡ በመጀመሪያ  ሥራቸውን ሀ ብለው የጀመሩት የሕዝባችንን አንድነትና ታሪክ ማፍራረስ ነው።

በአንድነት የኖረውን ሕዝባችንን አንድነቱን ለማሳጣት ያደረጉት ጥረት ተሳክቶላቸው መቅኖ

እንዳሳጡን ለማንም ኢትዮጵያዊ ግልጽ ነው። ሠላም ወዳዱና አንድነቱን አክባሪ የኢትዮጵያ ሕዝብ

የትግሬ ወያኔ ሥልጣን ከጨበጠ ጊዜ አንስቶ የሚያደርገውን አገርን የማፍረስ ሥራ አቅሙ በፈቀደው መጠን ሲታገለው ቆይቷል። የትግሬ ወያኔም ኢትዮጵያዊያንን ከመግደልና ከማዋረድ ውሎ ያደረበት ቀን የለም። ሞትና ውርደት ያንገበገባቸው ጀግኖች ኢትዮጵያዊያን “ቀለብ ከወገን ትጥቅ ከጠላት” የሚለውን መፈክር አንግበው በየክልላቸው ፋኖና የጎበዝ አለቃ በሚል ስያሜ ተቀናጅተው ወደ ትግል አምባ መጉረፍ ጀመሩ። አፍኖ በትውልድ መንደሩ ሊገድለው የመጣውን ወያኔ አፈርድሜ እያስጋጠ

ኃይሉን አጠናክሮ ትግሉን ቀጠለ። ፋኖ እና የጎበዝ አለቃ ኣንድ ሕዝብ አንድ አገር በሚል መፈክር በአረንጓደ ቢጫ ቀይ ያሸበረቀውን የኢትዮጵያ ሰንድቅ ዓላማ አንግበው በየጎራውና በየሸንተረሩ ተሰማሩ።

የኣገር ፍቅር ያንገበገውና እንደ ውኃ ነፃነት የተጠማው ጎበዝ ያገኘውን የማጥቂያ መሣሪያ ሽጉጦ ወደ ጫካው ተመመ ፤ ባዶ እጁን በቆራጥነት ወደ ትግሉ ጎራ በተጓዘ ሣምንት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ባለመሣሪያ ሆነ።

ትግሉም ጎመራ! በአፋሽ ወያኔ የኢትዮጵያ መሬት የተቸረው የሱዳን ወታደር ታጥቆ ወደ ጀግናው የኢትዮጵያ መሬት የኳተነው ትጥቁን ለፋኖ እና ለጎበዝ አለቆች አስረክቦ ወደመጣበት ሲፈረጥጥ ፤ጀግኖቻችን ከበቂ በላይ የታጠቀውን የትግሬ ወያኔ ለሆዱ አዳሪ ሠራዊት ትጥቅ ለማስፈታት ቋምጦ ወደ ፋኖና ወደ ጎበዝ አለቆች ሄዶ ሲመለስ ትጥቅ አስፈትቶ ሣይሆን የጓደኞቹን ሬሣ አቅፎ መሣሪያ የጠማውን ጀግኖች በተጨማሪ አስታጥቆ መመለሱን ሲያዩ ለአርበኞቻችን የበለጠ ሞራል እየሰጠ ሄደ። ፋኖ እና የጎበዝ አለቆች አፈሙዛቸው ያነጣጠረው በወያኔ የእንጀራ ወታደር ወይም የሆድ ተታላይ ብቻ ሣይሆን በወያኔ ደጋፊዎችና በሰላዮቻቸውም ላይ ነው።

ውድኢትዮጵያውያን!!

በዛሬው ዕለት የምናቀርበው ሪፖርት ዝርዝር ጉዳዮችን የያዘ ሣይሆን እንቅስቃሴያችንንና ትግላችንን

የሚመለከቱትን ብቻ ነው። በእርግጥ ጠላትን ለማጥቃት የሚደረገው ዝርዝር ሪፖርት ደካማ ጎን ቢኖረውም በሕዝባችን ደጀንነት ስለምንተማመን መገለጽ የሚገባቸውን ከዚህ በመቀጠል የምንገልጽ ሲሆን፤ የገድሉ አቀራረብ በቅደም ተከተል አይደለም። ምክንያቱም ትግሉ ከየሥፍራው ስለሆነና በጣም ተደራራቢ በመሆኑ ነው።

፩ .   በተለያዩ ቀበሌዎች ለወያኔ ተገዢዎችና ፊርማቶሪዎች ማስጠንቀቂያ በመስጠት የትግሬ ወያኔዎችና

ግብረ አበሮቹ የፋኖና የጎበዝ አለቆች እንቅስቃሴ ምስጢሩ እንዲጠበቅ ተደርጓል።

፪. የተሰጣቸውን ማስጠንቀቂያ ባለመቀበል ከወያኔ ጋር በማበር ሕዝባችንን በማሰቃየት ላይ ያተኮሩትን አስወግደዋል። ግለሰቦቹ እነማን እንደሆኑ ሕዝባችን ስለሚያውቀው እዚህ ላይ

ከመግለጽ እንቆጠባለን።

፫.   የወያኔን አፍራሽ አስተዳደር መከታ በማድረግ ሕዝባችንን በሚበድሉት ላይ የማያዳግም እርምጃ

ተወስዷል። ለዚህ ምሳሌ መጥቀስ ቢያስፈልግ በወሎ በባለብዕርፈራጅና በባለ ሽጉጥ ገዳይና በጎንደር ውስጥ ሐኪም ነኝ ባይ ለወያኔ ቀኝ እጅ ሆኖ ይሠራ በነበረው ላይ የተወሰደው የአደባባይ እርምጃ፤ እንዲሁም በወልድያ ሆተል ቤቱን በወያኔ ክላሽንኮቭ ያጨቀው ነጋዴ ውስኔ የተሰጠው በአርበኞቻችንና በሕዝባችን ሕብረት ነው።

፬. አርበኞቻችን ለሕዝባችን አንድነትና ለአገራችን ልዕልና ቆርጠው የተነሱ ስለሆነ የትግሬ ወያኔና

ቱልቱላዎቹ በተሰማሰሩበት ቦታ ሁሉ እየተከታተለ እያደባያቸው ነው።

ለዚህ ምሳሌ ቢያስፈልግ በሰሜናዊው አገራችን በመተማ ከአንድ ቡና ቤት ቀንደኞች የወያኔ አባሎች

ተሰብስበው ሲያሴሩ ለአርበኞቻችን መርጃው ደርሷቸው ጃኑዋሪ 6 ቀን 2018 ዓ ም ወደ ቦታው

ገስግሰው በመሄድ ወያኔዎቹ ስብሰባ ላይ እንዳሉ ሰባት የትግሬ ወያኔዎችን ገድለው ፤ ሲወያዩበት የነበረውን ሠነድ ይዘው አንድም ሰው ሣይጎዳባቸው በሠላም ወደ ወረዳቸው ተመልሰዋል።

እንዲሁም በዚያው በሰሜን ጎንደር ወያኔዎች ወጣቶችን የሚያሰቃዩበት የጦር ሠፈር በጅግኖቻችን በወሰዱት ቆራጥ እርምጃ ሙሉ በሙሉ ወድሞ ሠራዊቱም ደብዛው ጠፍቷል። ለዚህም ምስክሩ የአከባቢው ነዋሪ ሕዝባችንን መጠየቅ ይቻላል።

፭ . አርበኞቻችን የታጠቁት ከካሃዲውና ከአረመኔው የትግሬ ወያኔ ወታደርና ከገልጃጃው የሱዳን ወታደሮች እንደሆነ ማንም ሰው የሚያውቀው ሲሆን፤ ጀግናው ሕዝባችን በደሙና በሬውን ሽጦ የገዛውን መሣሪያ ሊያስፈታ በኮማንድ እዝ ታዝዞ የመጣውን ቅጥረኛና አፋኝ ወታደር መሣሪያዬ ወይም ሕይወቴ ብለው የቆረጡ ጀግኖቻችን የትግሬ ወያኔን እየረፈረፉ ፣ የተመቻቸው ሾልከው በሌላ አቅጣጫ ትግሉን ሲያጧጡፉ በጠላት ወያኔ የተከበቡ ደግሞ ታሪካቸውን ለትውልድ አደራ ሰጥተው አልፈዋል። ለዚህ ምሳሌ ሆነው ከሚጠቀሱ መካከል ጀግናው የመቶ አለቃ ደርቤ አየለ አንዱ ሲሆኑ ትጥቃቸውን ሊያስፈታ ከተጓዘ ከወያኔ መንጋ ጋር ጦርነት ገጥመው 13 ወታደሮችን ገድለው፤ ከ30 በላይ አቁስለው ጥይት ስለአለቀባቸው እጄን ለጠላት ውያኔ አልሰጥም በማለት ታሪካቸውን በደም ቀለም ጽፈው የጀግና ሞት ሞተዋል።

፮ . በመጋቢት ወር በዳባት ወረዳ ከአንድ ሠርግ ድግስ ታዳሚውን መሣሪያ የያዘ ይመጣል ተብሎ ስለተወራ በርካታ የወያኔ የኮማንድ ፖስት ወታደሮች ወደ ሠርጉ ቤት መሄዳቸውን የሰሙ አርበኞቻችን ወደ ቦታው ተጉዘው በመሄድ ተኩስ ከፍተው ሁለት የወያኔ ወታደሮችን ስለገደሉ የቀሩት ወደ

ኮማንድ ፖስቱ በመሄድ ኃይል በማጠናከር ወደ ሠርጉ በመመለስ ታዳሚውን ቢያንገላቱም አርበኞቻችን ግዳጃቸውን ተወጥተው በሠላም ወደ ወረዳቸው ተመልሰዋል። በዕለቱ የተግደሉ የወያኔ ወታደሮ ሁለት ሲሆኑ ብዛት ያላቸው እንደቆሰሉ ሕዝቡ ጠቁሞናል።

፯. በሚያዝያ ወር መግቢያ ላይ መነኩሴው በሚል የቅጽል ስም የሚታወቅ የፋኖ  የአመራር አባል ከወያኔ ወታደሮች ውጊያ ገጥሞ በርካታ ወያኔዎችን ረፍርፎ ከእግሩ ላይ በመቁሰሉ መታኮሻ ቦታ ይዞ ሲታኮስ የወያኔ ወታደሮች ከኋላው በኩል ቀርበው የእጅ ቦንቦችን ወርውረውበት ተሰው[illegible]ል።

፰. በወሎ፣ በጎጃም፣ በጎንደርና በሰሜን ሸዋ በርካታ አባሎቻችን የወያኔ አረር ሰለባ ቢሆኑም እጥፍ ድርብ ከታጠቀው የትግሬ ሠራዊት ትጥቅ እየቀሙ ዛሬ ከወያኔ ባልተናነሰ ታጥቀዋል ቢባል ማጋነን አይሆንም። በውያኔ አምባገነን አመራር የታሰሩ በአርበኞቻችን ኃይል በአብዞኛው ነፃ እየወጡ ናቸው። በኦሮሚያ ያሉትም እየተጠናከሩ ናቸው።

በኢኮኖሚ መስክ፡-

ይህን ሁሉ ግዙፍ የአገር ጉዳይ ለማንቀሳቀስ አመራሩም ሆነ ሕይወቱን መስዋዕት የሚያደርግ አርበኛ ከማንም ግለሰብ ወይም ድርጅት እስካሁን ድረስ ምንም ነገር እንዳላገኘ ማንም የሚያጣው አይደለም።ሌላው ቀርቶ በየዕለቱ ስለሚገኙ ገድሎች ለኢትዮጵያ ሕዝብ ለማሳወቅ የአየር ሞገድ የፈቀዱልን በጣም ጥቂት ጣቢያዎች ናቸው። ዛሬ በምክርም ሆነ በሃሣብ የሚተባበሩን የኢትዮጵያ የቀድሞ ሠራዊት አባላት ብቻ ናቸው። በአሁኑ ወቅት ወያኔንን የሚያክል ግዙፍ ጠላት መቅኖ ያሳጡት አርበኞቻችን በቆየው የአባቶቻችን ወኔ ነው። ትግላችን ወያኔ ተወግዶ የኢትዮጵያ ሕዝብ የራሱ መሪ እስከሚመርጥ ድረስ ቀጣይ ነው። ትግላችን እንዲፋጠን

በኃላፊነት ስሜት የሕሊና ወቀሳ አድሮበት በትጥቅና በኢኮኖሚ የሚተባበረን ወገን ከተገኘ እንቢ አንልም። የአርበኞቻችን አቋም ግልጽ ነው። ግለሰቦችን በማታለል ወሬ የሚገዙና የሚያናፍሱ ከአሁን በኋላ ቦታ እንደማይኖራቸው ነው። ገድለናል፣ እስረኛ አስፈትተናል፣ በለሳ ውስጥ ሰሜን ዕዝ ወታደር አቋቁመናል፣ ብለው የሚዘላብዱ ከአሁን በኋላ ቅንጣት ወሬ እንደማያገኙ እናረጋግጣለን።

ማኅበራዊና አስተዳደርዊ፦

ቆራጡ ሰራዊታችን ከትግሬ ወያኔ ሠራዊት ላይ በሚሰነዘረው ጥቃት ቢማረኩ ወይም ቆስለው ቢያዙ ወደ ሰዋራ ቦታ በማግለል የህይወት ታሪኩችውን በመመርመር ትምህርት በመስጠት እንደሁኔታው ይለቀቃል እንጂ ጠላት ነው ተብ። በየትምህርት ቤት የሚገኝ ወጣትም በትግሉ ላይ ብቻ ሣያተኩር መደበኛ ትምህርቱንም እንዲከታተል እንመክራለ።

በከተሞች የሚገኙ ወጣቶች የወያኔን ምስጢራዊ ሤራ እንዲከታተሉና እንዲያመክኑ መመሪያ ይሰጣል።በተለይ ወያኔ በሚጠራው ስብሰባ ላይ እንዳይገኝ ለወያኔ ገቢ ከሚያስገኙ ተቋማት አለመሳተፍ፣ ለወያኔ ገቢ ከሚያስገኙ እንደ የኳስ ሜዳዎች መራቅና ሰላዮችን ማጋልጥ ወዘተ ናቸው።

በመጨረሻም ለሐቀኛ ኢትዮጵያውያን በሙሉ የምናስተላልፈው የትግል ጥሪ የተናጠል ትግል ከየትም እንደማያደርስና ትግሉን የሚጎዳ መሆኑን በመገንዘብ በጋራ እንድንታገል ከዚህ በፊት ያቀረብነውን የአንድነት ጥሪ ወደ ተግባር በአንድ ላይ እንድንተረጉመው በድጋሜ የእንተባበር ጥሪያችንን እንላለን።

ዛሬ የኢትዮጵያ የመከላከያ ሠራዊት እናዋቅራለን፣ የፖሊስ ሠራዊት እንመሠርታለን፣ ገለልተኛ ዳኛ እንሰይማለን፣ የሽግግር መንግሥት

እናዋቅራለን፣ወዘተ የሚባለው የተስፋ ንግስና ሁሉ ለወያኔ የእድሜ ማራዘሚያ እንጂ ለተጀመረው የትንቅንቅ ትግል ከግብ እንደማያደርስ የታወቀ ነው።

ከሓዲ ወያኔ የአገራችንን መሬት ለባእዳን አሳልፎ መስጠቱን በማውገዝ የኢትዮጵያ የድንበር ኮሚቴ እንዲጠናከር የብኩላችን አስተዋጽዎ ለማድረግ ዝግጁነታችንን በደብዳቤ ለኮሚተው ገልፀናል።

*<u>በሪፖርተራችን ማጠቃለያ ላይ የምናሳስበው ካሉን ክምችቶች አንዱን ኦዲዮ (AUDIO) እንዲታዳምጡ በ ት ኅ ት ና እ ን ጋ ብ ዛ ለ ን !!</u>*

# *[ለመስማት ይህን ይጫኑ]*

*<u>አንድነታችን ለዘላለም ተከብሮ ይኖርል!!</u>*

<u>ትግላችን ያለ ጥርጥር ግቡን ይመታል!!</u>

<u>የኦሮሞ ሕዝብ ንቅናቄ ለኢትዮጵያ አንድነት</u>

<u>የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ</u>



EPNP.INFO

የኢትዮጵያ ሕዝብ ብሔራዊ ፓርቲ
ETHIOPIAN PEOPLE NATIONAL PARTY